# ወሳሳ ማይክሮፋይናንስ አክሲዮን ማህበር

## የባለአክሲዮኖች 30ኛ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድ ህግ አንቀጽ 366(1)፣ 367(1)፣ እና 370 መሠረት የወሳሳ ማይክሮፋይናንስ አ.ማ የባለአክሲዮኖች 30ኛ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ታህሣስ 21 ቀን 2018 ዓ.ም ከጠዋቱ 4:00 ሰዓት ጀምሮ በአዲስ አበባ ኤልጌል ሆቴል ይካሄዳል። በመሆኑም የተከበራችሁ የአክሲዮን የማህበሩ ባለአክሲዮኖች በዕለቱ በጉባዔው ላይ እንድትገኙልን የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያስተላልፋል።

### 1. ማህበሩን የሚመለከቱ ዋና ዋና መረጃዎች

የማህበሩ ዋና መ/ቤት አድራሻ፡- ኦሮሚያ ክልል፣ ሸገር ከተማ፣ ፋሪ ክ/ከተማ ጨፌ ከራቡ ወረዳ

ስ.ቁ. 011-338-41-33 ድረ-ገጽ https://www.wasasamfi.com የኢብባ ፈቃድ ቁጥር፡- MFI/017/2000

የተከፈለ ዋና ገንዘብ ብር፡- 10,000,000.00

### 2. የ30ኛው ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች

የጉባዔውን ድምጽ ቆጣሪዎች እና ጸሐፊ ከተሰየሙ በኋላ

2.1. የእለቱን አጀንዳዎች ተወያይቶ ማጽደቅ

2.2. እ.ኤ.አ የ2024/2025 የሂሳብ አመት የተደረጉ የአክሲዮን ዝውውሮች ማሳወቅ እና ማጽደቅ

2.3. እ.ኤ.አ የ2024/2025 የዳይሬክተሮች ቦርድን ዓመታዊ ሪፖርት ማዳመጥ

2.4. እ.ኤ.አ የ2024/2025 የውጭ ኦዲተርን ዓመታዊ ሪፖርት ማዳመጥ

2.5. በተ.ቁ. 2.3 እና 2.4 የቀረቡ ሪፖርቶችን ተወያይቶ ማጽደቅ

2.6. እ.አ.አ የ2024/2025 የተጣራ ትርፍ ድርሻ ላይ የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ ተወያይቶ ማጽደቅ

2.7. የዳይሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ የሥራ ዋጋን መወሰን

2.8. ተተኪ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሹመትን ማጽደቅ

2.9. የዳይሬክተሮች ቦርድ ያገዱዋቸውን ባለአክሲዮን ጉዳይ ላይ ተወያይቶ መወሰን

### 3. ማሳሰቢያ

3.1. በጉባዔው ላይ መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች ተወካዮቻችሁ ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ የተሰጠ የውክልና ሰነድ ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ በመያዝ ወይም በንግድ ህግ ቁጥር 377 መሠረት ጉባዔው ከመካሄዱ ከሦስት ቀናት በፊት ሰበታ አለምገና በሚገኘው ዋናው መ/ቤት በአካል በመቅረብ ለዚሁ ዓላማ በማህበሩ የተዘጋጀውን የውክልና ቅጽ ሞልተው በመፈረም ተወካይ መሾምና ተወካዩም የውክልና ማስረጃውን በመያዝ የጉባዔው ተካፋይ ለመሆን እና ድምጽ ለመስጠት የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን።

3.2. የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በጉባዔው ላይ ለመሳተፍ ሲመጡ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፍቃድ ዋናውን እና ኮፒውን (አንዲሁም ለወኪሎች አስፈላጊውን ህጋዊ የውክልና ማስረጃ ዋናውን እና ኮፒውን) በመያዝ በጉባዔው ላይ መሳተፍ ይችላሉ።

3.3. ሥልጣን ባለው የመንግሥት አካል በተሰጠ ውክልና በጉባኤው ላይ መገኘት የሚፈልጉ ተወካዮች በጉባኤው ለመሳተፍ እና ድምጽ ለመስጠት የሚያስችል የውክልና ሰነድ ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ ይዘው መቅረብ አለባቸው።

**የወሳሳ ማይክሮፋይናንስ አ.ማ የዳይሬክተሮች ቦርድ**

WASASA MICROFINANCE S.C.